# ያዉና ካራ ማራ ካራ ማራ ያዉና ጅጅጋ !!

Tedla Asfaw <tedla.asfaw@gmail.com>

ያውና ካራ ማራ ካራ ማራ ያውና ጅጅጋን ዘፈን በሰማው ጆሮዬ  ለስራ ከአንድ ፈረንጅ ጋር ስሄድ በካራ ማራ ሠንሠለት ተራራ የተከበበችዉን ጅጅጋ አይቼአታለሁ የዛሬ 35 ዐመት ገደማ። ክብር ሲያድ ባሬን መስፋፋት ዕብሪት ላስተነፈሱት የኢትዮጵያ መለዮ ለባሾች።

በአለም ማያ ኮሌጅ ከጦርነቱ በኋላ ይጠብቁን የነበሩት አባት ጦርና ኩባ ወታደሮች ያስተማሩን ሀገር ፍቅርና ከሀረር ራዲዮ ጣቢያ ይተላለፍ የነበረዉ የ ኪዩባ ዘፈን ና ኪዩባ ወታደሮች ዳንስ ትዝታው አይጠፋም።

ከሞቃዲሾ ይተላለፍ የነበረው የአማርኛ የሲያድ ባሬ ፕሮፓጋንዳ የተመሰረተው የዘር ጥላቻ አሁንም በሀገራችን ምስራቅ ኢትዮጵያ በኦሮሚኛ ተናጋሪዎች መቀጠሉ አያስገርምም።

የሲያድ ባሬ ራዲዮ ከሞቃዲሾ እንዲህ ይል ነበር እስካሁን የማልረሳው። ቁጭራው መንግስቱ ኃይለማርያም እንደ ቅኚ ገዢ አባቱ ምኒልክ መሬትህን የቀማውን ተዋጋው።

የሶማሌ አቦ እያለ ሲያድባሬ ኦሮሚኛ ተናጋሬዉን ሶማሌ አጋዴን ሶማሊኛ ተናጋሪዉን ለታላቅዋ ሶማሊያ ምስረታ ከኢትዮጵያ ጋር ላደረገው ጦርነት የባዕዳን ዕርዳታ በሰጠው የበላይነት የኢትዮጵያን አብዮት ተንተርሶ ባለው ዉስጣዊ አለመረጋጋት ጊዜያዊ ድል አግኝቶ ነበር።

ባለፉት 28 ዐመት የተጎዘንበት የ ጎሳ ፌዴራሊዝም አሁን በምስራቅ ኢትዮጵያ ለተፈፀመው መፈናቀል ሀረርና ድሬዳዋላይ ያለው  ዉጥረት ሁሉ ሲያድ ባሬ የዛሬ አርባ ዐመት በፊት ከሞከረዉ ጋር ይያያዛል።

ሶማሌ  አቦ ዛሪ ኦሮሚያ ኢስላሚያ ነው። ኦሮሙኛ የሚናገረዉን ሁሉ ያለበት ኦሮሚያ እያለ መሬት ይቀማል።
ኦነግ ድሬዳዋ የኔ ነው ይላል ሲያድ ባሬ ከአዋሽ መልስ ሶማሌ አቦ እንደሚለው ሀረርን ጨምሮ።

ሲያድ ባሪ የራሱን ሶማሌ ለማያባራ ጦርነት ትቶ ቢያልፍም የዘራው ፀረምኒልክ ጥላቻ በ " Oromo First" ና በ ኦነግ መሪነት ድሬዳዋና አዲስ አበባን ጨምሮ ታላቅዋን ኦሮሚያ ለመመስረት በአዲስ አበባና ወለጋ እያሸበረ ይገኛል።

ይሄ ትዉልድ ሰሞኑን የአድዋ 124ኛው ድል በአዲስ አበባ ሲዘከር ያሳየዉ አንድነት በድሬዳዋ ሶማሌ ኢትዮጵያዉያን በጅጅጋ የምናየዉ ኢትዮጵያ የሁላችን በዕኩልነት ትግል የኦሮሞ ተስፋፊዎችና ኦሮሞ ሪፐብሊክ አቀንቃኞች ለሰሞኑ ታፈን ጩኸት ዋናው ምክንያት ነው። ኢትዮጵያ አንድ ሀገር ሆና ትቀጥላለች።

በምሥራቅ ኢትዮጵያ የተሠዉት የሀገራችን ልጆች ለሀገር ዳር
ድንበር  ለሌሎቻችን መኖር ምክንያት በመሆናቸው ሁሌም እናስባቸዋለን።

እኛም ለሀገር ልዑላዊነት በቋንቋ ሀይማኖት ሳንለያይ እንዳለፉት ኢትዮጵያውያን የሚገባንን ድርሻ እንወጣለን።